## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

ሐምሌ 6፣ 2004ዓም

# ከህወሓት/ኢህአዴግ በኋላ፡ የኢትዮጵያችን ዕጣ ፈንታ

ካለፉት ጥቂት ሳምንታት ጀምሮ በተለያየ ጊዜያት ሁላችንም ለመመልከት እንደቻልነው አቶ መለስ ጤናቸው ክፉኛ ተቃውሷል፡፡ በተለይ በሜክሲኮ የተካሄደው የቡድን 20 አገራት ስብሰባ ላይ የቻይና የዜና አገልግሎት ያሳየን ምስል በእርግጥ ላለፉት 21 ዓመታት ባናውቃቸው ኖሮ አቶ መለስ ለመሆናቸው እንድንጠራጠር የሚያደርግ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ ላይ አለመገኘታቸው እና እስካሁን ከህዝባዊ መድረክ የመሰወራቸውን ምክንያት ለሕዝቡ ከማስረዳት ይልቅ "የሕዝብ ድምጽ" በሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ የዕድሜ ልክና የረጅም ዓመታት ፍርድ መፈረዱን ለሕዝቡ ማወጅ ህወሓት/ኢህአዴግ በራሱ ላይ የመጨረሻ ፍርድ እንደወሰነ የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ከመቼውም ይልቅ ኢትዮጵያ እጅግ ውስብስብ በሆነ ችግር ውስጥ እንደምትገኝ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሲሆን የአገራችን መጻዒ ዕድል በአንድ ሰው መኖርና አለመኖር ላይ ሳይሆን አስቀድሞ በተጠናና በተዘጋጀ ዕቅድ ላይ መመሥረት እንዳለበት ያምናል፡፡ **ይህ ብቻ አይደለም፤ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ልትመሠረት የሚገባት በ"ሰርገኛ መጣ..." ስሌት ሳይሆን "ከዘረኝነት ይልቅ ለሰብዓዊነት" ልዩ ትኩረት በሰጠ፤ ሁሉን ዓቀፍ ዕርቅን መሠረት ባደረገና በሰከነ መንፈስ መሆን እንዳለበት የጋራ ንቅናቄያችን በጥብቅ ሲያስገነዝበው የኖረ ጉዳይ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡**

የጋራ ንቅናቄያችን የዛሬ አራት ዓመት ከመቋቋሙ በፊት በአኙዋክ የፍትሕ ምክርቤት የነበሩ ጥቂቶች በኢትዮጵያ ዘላቂ ፍትህና ሰላም ለማምጣት ዓይነተኛው አማራጭ በዘር ተደራጅቶ መታገል ሳይሆን የሥርዓት ለውጥ ማምጣት እንደሆነ በውል እየተረዱ የመጡበት ጊዜ ነበር፡፡ በወቅቱም የቅንጅት አመራሮች ከእስር ከተፈቱ በኋላ በመካከላቸው የተፈጠረውን ልዩነት አቻችለው ቢያንስ የሕዝቡን ሞራል ለመጠበቅ ሲባል ትግሉን እንዲቀጥሉ የሚያሳስብ መልዕክት በፍትሕ ም/ቤቱ ስም ተልኮ አስፈላጊም ከሆነ ም/ቤቱ ለመሸምገል ፍላጎቱ እንዳለው ሃሳብ ማቅረቡ የብዙዎች ትዝታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የም/ቤቱ የመፍትሔ ሃሳብ ቅንጅት ከደረሰበት ቁስል አገግሞ በአዲስ መልኩ ሁሉን ዓቀፍ የትግል ስትራቴጂ በመንደፍ በተጠናከረ ሁኔታ ትግሉን ይቀጥላል የሚል ነበር፡፡ ሆኖም ሁላችንም እንደምናውቀው ቅንጅት ኅልውናውን አጣ፤ አመራሩም ተበታተነ፡፡

ከዚህ በኋላ ነበር የዛሬ አራት ዓመት በም/ቤቱ ውስጥ የነበሩ ጥቂቶች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄን (አኢጋን) የመሠረቱት፡፡ ከጅምሩም የጋራ ንቅናቄው መሠረታዊ ዓላማ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ የዘር፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ የሃይማኖት፣ ወዘተ ልዩነት ሳያደርግ የትብብር እንቅስቃሴ ማድረግ ነበር፡፡ **ሆኖም አንዳንዶች በተሳሳተ መልኩ አኢጋንን እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አድርገው ቢቆጥሩትም የጋራ ንቅናቄው ዋና ዓላማ ግን የሰዎችን አስተሳሰብ (የህወሓት/ኢህአዴግንም ጨምሮ) መለወጥ ላይ ያተኮረ እንደነበር ከጅምሩ ገና ሲቋቋም የገለፀው፣ ዛሬም አበክሮ የሚደግመው አንኳር ጉዳይ ነው፡፡** በመሆኑም የአቶ መለስ አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን ግፍ ከማጋለጥና ለዓለም ከማሳወቅ ባለፈ መልኩ በተቃዋሚውም ጎራ በተለይ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በእስር በነበሩበት ወቅት በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የተፈጠረውን ክፍፍል አስመልክቶ አመራሮቹን በግል ከማነጋገር ጀምሮ በግልጽ ደብዳቤ በመጻፍ ስምምነት ላይ መድረስ የሚችሉበትን መንገድ እንዲቀይሱ ማሳሰቡና ማስገንዘቡ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ በህወሃት/ኢህአዴግ አመራር ውስጥ ያሉትም ሃሳባቸውን ወደ ህዝብ እንዲመልሱና ራሳቸውን ከእኩይ ተግባር በማቀብ ለለውጥ እንዲያዘጋጁ በተከታታይ መልዕክት ሲልክ እንደነበር የመልዕክቱ ተቀባዮች ጭምር የሚመሰክሩት እውነት ነው፡፡

የዛሬ አርባ ዓመት አካባቢ ንጉሣዊው አገዛዝ በሕዝባዊ አመጽ በወደቀበት ጊዜ በሥልጣን መስመር ላይ የተሰለፉት በርካታዎቹ ግራ ዘመም የሆነውን የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚከተሉ በመሆናቸው የአዲስ ስርዓት ግንባታ በመቻቻልና በዕርቅ ሳይሆን "በጠላቶቻችን መቃብር ላይ መሆን አለበት" የሚል መርህ በመከተላቸው የበርካታ ንጹሐን ደም በከንቱ ሊፈስ ችሏል፡፡ በዘመነ ደርግም ወደመጨረሻው አካባቢ የዕርቅና ሰላም ሃሳብ ቢነሳም በዚያው በግራ ዘመም አስተሳሰብ የተጠመቁት አብዮተኞች አርቆ ማሰብ ባለመቻላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሌላ መከራ ተመቻቸ፡፡ አጋጣሚውን መጠቀም ባለመቻሉ በዘር ላይ የተመሠረተውና አክራሪ ኮሙኒስት የሆነው ህወሓት የኢህአዴግ ካባውን አጥልቆ የስልጣን እርከን ላይ ተቆናጠጠ፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ "በጠላቶቹ መቃብር ላይ" ሌላ እሱ የሚፈልጋትን ኢትዮጵያን ለመመሥረት በወሰደው እርምጃ ከደርግ በከፋ መልኩ "የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል" በሚል መፈክር የኢትዮጵያን ጥፋት እጥፍ ድርብ አደረገው፡፡ ይህ ሲሆን የንጉሣዊው አገዛዝ ሲወርድ የተነሱት በግራው አስተሳሰብ ምለው የተጠመቁት የዘርና ኅብረብሔራዊ ድርጅቶችም በዚሁ "የራስን ዕድል በራስ መወሰን" የሚለው አመለካከት አራማጅ በመሆናቸው ያሰሙት ተቃውሞ አልነበረም፡፡

ሁኔታው የተመቻቸለት ህወሓት/ኢህአዴግም ያለ አንዳች ችግር ኤርትራን ካስገነጠለ በኋላ የትግራይ ተወላጆችን በተጋዳላይ ስም እንዲሁም በጥቅም፣ በቤተሰብነትና በሥልጣን በመደለል መቀመጫውን ማደላደሉን ተያያዘው፡፡ አስቀድሞ የተጠቀመባቸውን ግራም ሆነ ቀኝ አመለካከት የያዙትን ሁሉ ባፋጣኝ ከአካባቢው በማጥፋት የትግራይን የበላይነት ማስተጋባቱን ቀጠለበት፡፡ ይህም በበርካታውና ወደ ጎን ገሸሽ በተደረገው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ብስጭት፣ ጥላቻና ቂም እንዲቋጥር እያደረገው መምጣቱ የሚስተዋል ሆነ፡፡ የፖለቲካውን፣ የኢኮኖሚውን፣ የማኅበራዊውን፣ ወዘተ ምህዳር ራሱ በሚፈልግበት መልክ ሲያጠብና ሲያሰፋ ቆይቶ በረሃ የለመደውን ህንፍሽፍሽ በድጋሚ በማንሰራራት በሙስና ስም የበረሃ ባለውለታዎቹን "በላቸው"፡፡ በቀጣይም በአቶ መለስ ዙሪያ ፍጹም ታዛዥ የሆኑ አመራሮችን በማሰባሰብ "የቅብብሎሽ መተካካት" ድራማ የተጀመረ ሲሆን ከፋፍሎ ለመግዛት ያመች ዘንድ የበረሃ ተሞክሮ የሌላቸውን ጥቂት "ምሁራን" ከበረኸኞቹ ጋር በማዛነቅ የተወሰደው እርምጃ አምልኮተ-መለስ እንዲፈጠር በማድረግ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል፡፡

ተመሳሳይ አምባገነናዊ አካሄድ ሲከተሉ የነበሩ የዓለማችን መሪዎች ኀልውናቸው ሊያከትም በሚቃረብበት ጊዜ ሁሉም ነገር ለመፈረካከስ እንደሚፍገመገም ሁሉ አሁንም በህወሃት ውስጥ በአቶ መለስ ደጋፊዎችና በውህዳኑ መካከል ካለው የሰፋ ልዩነት በተጨማሪ በግለሰብ ደረጃ ያለው ክፍፍል አቶ መለስ በጤናም ሆነ በሌላ ምክንያት ከስልጣን ከተወገዱ በኋላ በህወሓት/ኢህአዴግ ውስጥ ሁኔታዎች በፊት እንደነበሩት ይቀጥላሉ ማለት እንደማይቻል እሙን ነው፡፡ ለዚህም በርካታ ምልክቶችና ማስረጃዎች አሉ። ከዚህ ሌላ ለዘመናት ህወሓት ሲያስተጋባው የነበረውን የዘር ፖለቲካ የሚጻረረው የተቃዋሚ ኃይል በአጸፋ ይሰጥ የነበረው ምላሽ ተወደደም ተጠላ የትግራይ ተወላጆችን በጥላቻና በቂም ቀለበት ውስጥ እንዲገቡ ሲያደርጋቸው መቆየቱ የሚካድ አይደለም፡፡

በመሆኑም ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ በመመልከትና ካለፈው ተሞክሮ በመውሰድ የጋራ ንቅናቄያችን ከህወሓት/ኢህአዴግ በኋላ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምሥረታ የሚደረገው አካሄድ "የሰርገኛ መጣ..." ወይም "በጠላቶቻችን መቃብር..." ላይ መሠረት ያደረገ እንዳይሆን ዝግጅት እንደሚያስፈልግ ያምናል፡፡ ታሪክን የመድገም ግዴታ የተጣለብን አለመሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ በአገራችን ላይ ያለማቋረጥ እየተከሰተ ያለው የጥፋት አዙሪት ማብቂያው የሁሉንም የተቀናጀ አካሄድ ብቻ ሳይሆን የዕርቅን መራራ ጽዋ ለመጠጣት የተዘጋጀ ሆደ ሰፊነትንም ይጠይቃል፡፡ ለበርካታ ጊዜ በቡና ጀበና የምትመሰለው ኢትዮጵያችን ለሁላችንም የሚበቃ ጣፋጭ ቡና በውስጧ ይዛለች፡፡ ሁላችንም በትዕግሥትና በቅንነት የማንጠብቅ ከሆነ በ"እኔ ልቅደም" ወይም በ"ሳይቀድሙኝ ልቅደም" አካሄድ የምናደርገው እሽቅድምድም ጀበናው ተሰብሮ ቡናውን ማንም ሳይጠጣው እንዳይቀር የዕርቅ ጉዳይ ቀዳሚነት ሊሰጠው የሚገባ እንደሆነ የጋራ ንቅናቄያችን ያምናል፡፡ እምነቱም ዕኑ መሆኑን እንደወትሮው አስረግጦ ይገልጻል። ሁሉም አገር ወዳዶች በሰከነ ልቡና ይህንን አቢይ ጉዳይ እንዲመረምሩት ጥሪውን ያስተላልፋል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ለዓመታት በፈጸመው ጭካኔ የተሞላው ተግባር በርካታ ኢትዮጵያውያን በደረሰባቸው በደል ምክንያት “የመጣው ይምጣ ከዚህ በላይ የማጣው ነገር የለም” በሚል አስተሳሰብ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በመሠረቱ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ አፍራሽ ብቻ ሳይሆን አደገኛ በመሆኑም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያሻው ነው፡፡ በአንጻሩ በትግራይ ተወላጆች ዘንድም የዚህ ዓይነት ጥቃቶች ሰለባ እንሆናለን የሚለው አስተሳሰብ የገነነ ነው፡፡ በመሆኑም ከአቶ መለስ የሥልጣን መወገድ ማግስት የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ከምንጊዜውም ይልቅ የሁላችንንም ትኩረት የሚስብ ሆኗል፡፡ በመሆኑም በደቡብ አፍሪካና በሌሎች አገራት የተካሄደው ዓይነት ዕርቅና ስምምነት መቅደም ያለበት ብቻ ሳይሆን በተግባር መፈጸም ያለበትም ነው፡፡ ለዘመናት ህወሓት/ኢህአዴግ የተከተለው የ“እነርሱና እኛ” አስተሳሰብ ከዚህ በኋላም በዚሁ መልኩ መቀጠል የለበትም፡፡ ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ በሩዋንዳ ያስከተለውን በውል የምንረዳው ነውና፡፡ ይህንንም በማሰብ በተለይ የትግራይ ተወላጆች በድንጋጤና በጭፍንነት ሊወስዱ የሚያስቡት እርምጃ የትም የሚያደርስ ሳይሆን መልሶ እራሳቸውን ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ እንደሆነ እንመክራለን፡፡ ስለሆነም ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ በላቀ መልኩ የትግራይ ተወላጆች በመተማመን ላይ ለሚፈጸመው ዕርቅ ራሳቸውን ማዘጋጀት በቅድሚያ የሚጠበቅባቸው ይሆናል፡፡ በተለይም በህወሓት/ኢህአዴግ ውስጥ የምትገኙና የተመቻቸ አጋጣሚ ስትጠብቁ የነበራችሁ ሁሉ ከሕዝብ ጋር በመቆም ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምስረታ በገሃድ የምትሰለፉበት ወሳኝ ጊዜ አሁን ነው፡፡ በተቃዋሚው ጎራ የሚገኘውም ኃይል ሁሉ ይህንን መራር ግን የተቀደሰና በሳል የሆነ አካሄድን በሆደ ሰፊነት ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን ስንል በመቀበል አገራችን ከገባችበት አዙሪት እንድትወጣ በቂ ዝግጅት ልናደርግ ይገባናል፡፡

የጋራ ንቅናቄያችን ይህንን ሃሳብ ለበርካታ ዓመታት ሲያስተጋባ የኖረ እንደመሆኑ በሁሉም ዘንድ ተዓማኒነት ያለው ብቻ ሳይሆን በቂ ዝግጅትና ዕቅድም ያወጣ በመሆኑ እንደሁኔታው አስፈላጊነት ለሕዝባችን ወቅቱን ጠብቀን እንደምናሳውቅ እንገልጻለን፡፡ ከዚህም አንጻር ከሁሉም ኃይሎች ጋር ሁላችንንም ነጻ ሊያወጣ በሚችል መልኩ እንደምንሠራ ስንገልጽ ለዚህም የፈጣሪ እርዳታ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ጋር እንዲሆን እንመኛለን፡፡ በመልካምነትና በቅንነት ትክክለኛ ለሆነው ነገር አእምሮአችንን ስናስገዛ እውነተኛውን ነጻነት ሁላችንም እንጎናጸፋለን፡፡

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

*****************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአኢጋን ዋና ዳይሬክተር አቶ ኦባንግ ሜቶን (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

